# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን

# የቅርስ እንክብካቤ/ኮንሰርቬሽን/ ላቦራቶሪ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ

## ቁጥር 761/2013

ሐምሌ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የሀገራችን ቅርሶች ለተጨማሪ ሳይንሳዊ ጥናትና ተያያዥ ተግባሮች በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 27 መሰረት ከሀገር የሚወጡበትን ሂደት መቆጣጠርና በዚህም የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ በማስፈለጉ፣

በተለያዩ ጊዜያቶች ከደንበኞች/ተመራማሪዎች/ የሚነሱ ጥያቄዎችን በሙሉ በመመለስ ከተቋሙ የሚያገኙት አገልግሎት ፍትሃዊ እና ምቹ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፣

በዘርፉ ሀገራችንን ለማሳደግና ብሎም ለኢኮኖሚያዊ ግንባታ የሚጠበቅብንን ድርሻ በብቃት ለመወጣት አስተማማኝ መሰረት መዘርጋት ተገቢ በመሆኑ፣

የቅርስ እንክብካቤ ቤተ ሙከራው በቀጣይ በአፍሪካ ብሎም በአለም ላይ ዋና የምርምር እና ልሕቀት ማዕከል እና ከአቻ አህጉራዊም ሆነ አለም አቀፋዊ የምርምር ተቋማት ይበልጥ ተመራማሪዎችን እንዲስብ ማድረግ ስለሚያስፈልግ፣

ለተገልጋዮች ቀልጣፋ፣ወጪ ቆጣቢና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ፣

ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

**1. አውጭው ባለሥልጣን**

የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናት እና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሠጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**2. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የቅርስ እንክብካቤ ቤተሙከራ አገልግሎት መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**3. ትርጓሜ**

ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር 209/1992 ክፍል አንድ አንቀፅ 3 ላይ የተሠጠው ትርጓሜ በዚህ መመሪያ ላይም ተፈፃሚነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ትርጓሜ በመመሪያው ተካቷል፡-

1. **የቤተ ሙከራ ጥናት ፍቃድ፡-**

   ከቅርሶች ስብስብ ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ሣይንሣዊ ጥናትና ምርምር በስብስብ ክፍሉ የሚሰጥ ፈቃድ ማለት ነው፡፡

2. **ማመልከቻ**፡-

   ለጥናት ወይም ለካስት ስራ ወይም ለሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ የቅርስ ውሰት ወይም በአደራ ቅርሶችን ለማስቀመጥ የተዘጋጀውን ሕጋዊ ቅፅ በመሙላት በፅሁፍ የሚቀርብ መጠየቂያ ማለት ነው፡፡

3. **የቅርስ ስብስብ ቆጠራ** ፡-

   በየስብስብ ክፍሉ ያሉትን ማናቸውም ቅርሶችን ለመቆጣጠር ወይም ለጥናት ወይም ለጥገና ወይም ለእንክብካቤና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች ለማዋል የሚደረግ ወቅታዊ የመቆጣጠር ሂደት ነው፡፡

4. **ሞልድ**፡-

   በስብስቦች ለሚገኝ የቅርስ አይነት ቅጅውን ለማውጣት የዋናውን አሻራ ትክክለኛ ቅርፁንና መጠኑን በሚያሳይ መልኩ በቴክኒሽያኖች በኬሚካል ተሰርቶ የሚወጣ በዘላቂነት ካስት ለማባዛት የሚያገለግል የቅርስ ወካይ ማለት ነው ፡፡

5. **የሞልድና ካስት ቴክኒሽያን** ፡-

   ሞልድና ካስት የሚሰራ ባለሙያ ማለት ነው፡፡

6. **ሳይንሳዊ ካስት**፡-

በስብስቦች በሚገኝ የቅርስ አይነት ላይ ለሚደረግ ቀጣይ ሣይንሳዊ ጥናት የሚያግዝና የቅርሱን የቅርሱን ትክክለኛ ቅርፁን፣ያሉትን ምልክቶችና መጠኑን ሙሉ በሙሉ በሚያሳይ መልኩ ሞልዱን በመጠቀም በኬሚካል የሚሰራና የቅርሱ ወካይ ማለት ነው፡፡

7. **ኮመርሻል ካስት ፡**

በጥናትና ምርምር ከተገኙ ስብስቦች ውስጥ በመምረጥ ወካይ ሞልድ በማዘጋጀት ፍላጎት ላላቸው አካላት እየተባዛ ለሽያጭ የሚቀርብ ካስት ማለት ነው፡፡

8. **የንፅፅራዊ ሥነ አካል/ኮምፓራቲቭ አናቶሚ/**፡-

በአሁን ዘመን ያሉ እንስሳት አካል፣ እፅዋት እና ሌሎችም በባለሙያዎች ተሰብስበው በቀደምት ዘመን ካሉ የእንስሳት፣የእፅዋትና ሌሎችም ዝርያዎች ቅሪቶች ጋር የተከለ ሰውነት ንፅፅር ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የሚደራጁበት፣የዝግመተ ለውጥ፣የተላምዶ ሂደትና ሌሎችም ምርምሮችና ትንተናዎች የሚደረጉበት ክፍል ነው፡፡

9. **የንፅፅራዊ ሥነ አካል ቴክኒሽያን**፡

የንፅፅራዊ ሥነ አካል ክፍልን በአግባቡ የሚያዘጋጅ፣ የሚንከባከብና ለምርምሩ ድጋፍ የሚያደርግ ባለሙያ ነው፡፡

10. **የቅርስ ስብስብ ማዕከል**፡-

የተለያዩ ቅርሶች ተሰባስበው የሚጠበቁበት፣እንክብካቤ የሚደረግበት፣ የሚደራጁበትና ለቀጣይ ጥናትና ምርምር ዝግጁ የሚሆኑበት ክፍል ወይም ማዕከል ነው፡፡

11. **የቅርስ ምርምር** ፡-

በተለያዩ ዘርፎች በሚገኙ ስብስቦች ላይ የዕድሜ ቀመር ወይም ንፅፅር ወይም አካባቢያዊ ወይም የቅርሱን ቁሣዊ ሁኔታዎች በጥልቀትና በተጨባጭ ለማወቅ የሚደረግ ሣይንሣዊ ፍተሻና ጥናት ማለት ነው፡፡

12.**<u>የቅርስ ምርምር ቤተ ሙከራ</u>** ፡-

በተለያዩ ዘርፎች ለሚደረጉ የቅርስ እንክብካቤና ጥገና ወይም የዕድሜ ቀመር ወይም ንፅፅር ወይም ለሌሎች ጥናትና ምርምሮች አስፈላጊ የሆኑ ኢጋዥ ቁሣቁሶች የተሚሉለትና ምርምር የሚካሄድበት ክፍል ማለት ነው፡፡

13. **<u>አጥኚ/ተመራማሪ</u>**/፡-

በተለያዩ የቅርስ ስብስቦች ላይ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ ግለሰብ ወይም ቡድን ማለት ነው፡፡

14.**የቅርስ ተንከባካቢ (ኩሬተር)**:-

ከቅርስ ጋር ተያያዥ በሆነ ትምህርት የሰለጠነና የቅርስ ስብስብን የሚመራ፣ ቅርሶችን የሚንከባከብ፣ የሚያደራጅ፣ ለተመራማሪዎችና ተገልጋዮች የሙያ ድጋፍና አገልግሎት የሚሠጥ፣ ጥናትና ምርምር የሚያደርግ ባለሙያ ማለት ነው፡፡

15.**የቅርስ ዝግጅት ቴክኒሽያን**፡-

በተለያዩ ዘርፎች ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች ቅርሶችን እንዲያፀዱና ለጥናትና ምርምር ዝግጁ እንያደርጉ የሚቀጠሩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ባለሙያዎች ማለት ነው፡፡

16. **የሥነ ምድር ናሙና**:-

በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ለሚደረግ ለዕድሜ መለካትና የአለት ናሙና ምርምር እንዲሁም ለተለያዩ የጥናት ተግባራት እንዲውሉ ከተለያዩ የጥናት ስፍራዎች የሚመጡና ቅርስነት የሌላቸው ናሙናዎች ማለት ነው፡፡

17.**አውዳሚ ትንታኔ**:-

የተለያዩ ሣይንሣዊ መረጃዎችን ለማግኘት፣ዕድሜ ለመለካትና ለሌሎችም ጥናቶች ተግባር የሚውሉ ጥንታዊነት ያላቸው ወይም የሌላቸው የቅርሶች ናሙናዎች ማለትም ስብርባሪ አጥንቶች፣ ሸክላዎች፣ ጡቦች፣ ከሰል፣ እንጨት የእህል ዘር፣ ሞርታር፣ የብረት ዝቃጭ፣ የባልጩት ስባሪ እና የመሳሰሉትን የነበረ ይዞታቸውን በመቀየር፣ በመሰባበር፣ በማላም የሚደረግ ሣይንሣዊ የምርምር ዘዴ ማለት ነው፡፡

18.**የጥርስ መስታወት ናሙና ወሰዳ፡-**

ከቅርሱ የላይኛው የጥርስ ሽፋን/ENAMEL/ፍቅፋቂ ናሙና የመውሰድ ተግባር ነው፡፡

19. **ሕትመት**፡-

በመፅሐፍ ወይም በጆርናል ወይም በሞኖግራፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ሕትመት /e-book/መልክ የሚወጡ የጥናትና ምርምር ፅሁፎች ማለት ነው፡፡

20 . **የቅርስ መረጃ፡-**

ማለት የአንድን ቅርስ አጠቃላይ የቅርሱን ይዘት፣ዓይነት፣ ብዛት፣ ከየት ስፍራ እንደተገኘ፣በማን እንደተገኘ፣ በከምችት ክፍሉ በየትኛው ስፍራ እንደሚገኝ፣የቅርሱን አገኛኘት ዘዴ፣የተሰራበት ቁስ፣የቅርሱን መለያ ባህሪና የቅርሱን አጠቃላይ ሁኔታ ያካተተ መግለጫ ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ ውስጥ በሚሠጥ የቅርስ ቤተሙከራ አገልግሎት እና ከዚህ ጋር ተያያዥ በሆኑት ስብስቦች አገልግሎት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5. ስለ ፆታ አገላለጽ

በግልፅ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## 6. በቤተ ሙከራው የሚሰጡ ዋና ዋና አገልግሎቶች

1. ለተማሪዎችና ተመራማሪዎች የቤተ ሙከራ አገልግሎት ፣
2. የካስት አገልግሎት ፣
3. የናሙናዎች ፍቃድ፣
4. ቅርስን አስመልክቶ ስልጠናዎችን መስጠት፣
5. የምርምር ውጤት የሆኑ መረጃዎችን ማደራጀት፣ወደ መረጃ ቋት ማስገባትና መረጃ መስጠት ናቸው፡፡
6. ለክልል ሙዚየሞችና ኪዩሬተሮች የምክርና የተግባራዊ እገዛ ማድረግ ፤

## 7. ለተመራማሪዎች የሚሰጥ ፍቃድ

1. ማንኛውም አጥኚ በቤተ ሙከራ ጥናት ለማድረግ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ወይም በፖስታ ቤት ወይም በአካል ቀርቦ ምርምር ከመጀመሩ ከአንድ ወር በፊት በፅሑፍ ጥያቄውን ማቅረብ ይኖርበታል ፣
2. የቤተ ሙከራ አገልግሎት ፍቃድ ጥያቄ በአንድ ቀን ውስጥ ምላሽ ይሰጣል ፣
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ı የተጠቀሰው የጊዜ ቅድመ ሁኔታ የመስክ ፕሮጀክት ፍቃድ ተሰጥቷቸው እየሰሩ የሚገኙትን አይመለከትም ፣
4. በቡድን ቤተ ሙከራ ለመገልገል ጥያቄ የማቅረብ ኃላፊነት የጥናት ቡድን መሪዎች ይሆናል፣
5. ጥናቱን የሚያካሂደው ራሱ ተመራማሪው /አጥኚው/ ካሰባሰባቸው ግኝቶች ውጭ ባሉ ቅርሶች ላይ ከሆነና ጥያቄው የቅርሱ አግኚ የጥናት ፍቃድ ዘመን ሣይጠናቀቅ ከሆነ ከአግኚው የተሰጠውን የፅሁፍ ፈቃድ ማቅረብ አለበት ፣
6. አጥኚው የቤተ ሙከራ ጥናት አገልግሎት ጥያቄ ፍቃድ ሲያገኝ በአካል በመቅረብ በዳይሬክቶሬቱ የተዘጋጁትን ፎርሞች በሚመለከተው ኩሬተር በኩል ይሞላል ፣
7. የጥናት ክፍል ድልድል በሚዘረጋው ስርአት በሚመለከተው ኩሬተር ወይም ባለሙያ በኩል ይከናወናል፣
8. የተለያዩ ግለሰብ አጥኚዎች ወይም ቡድኖች በጋራ በአንድ ክፍል እንዲሰሩ የሚያስገድድ ሁኔታ ቢፈጠር ቅድሚያ ለመጣ መጀመሪያ አገልግት የሚሰጥ ቢሆንም የክፍሉ ኩሬተር ከአጥኚዎች ጋር በመነጋገር ሁኔታዎችን ያስተካክላል ፣

9. የቅርስና የሥነ ምድር ናሙናዎች ለተጨማሪ ሳይንሳዊ ጥናት /ለአውዳሚ ትንተና፣ለእድሜ መለካትና ለሲቲ ስካን ተግባሮች/ በአጥኚው በኩል ከስብስብ ወደ ውጭ ለማውጣት ከዳይሬክቶሬቱ ወይም ከባለስልጣኑ እንደደረጃው ፍቃድ ማግኘት አለባቸው ፤

10. ማንኛውም ተመራማሪ /አጥኚ/ ወይም የጥናት ቡድን አምስት አመት የሞላቸውንና ሕትመት ያልወጣባቸውን ግኝቶች ይህ መመሪያ በወጣ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ሕትመታቸውን ካላወጣ ባለስልጣን መ/ቤቱ በሌሎች አጥኚዎች /ተመራማሪዎች/ እንዲጠና ይፈቅዳል ፤

**8. <u>የተመራማሪዎች መብት</u>**

1. ከተለያየ የዓለም ክፍል የሚመጡና በሃገራችን የቅርስ ስብስቦች ላይ ጥናትና ምርምር ለማድረግ የቤተ ሙከራ አገልግሎት ጥያቄ የሚያቀርቡ ተመራማሪዎች/አጥኚዎች/ በጥያቄያቸው ቅደም ተከተል መሠረት ይስተናገዳሉ ፤
2. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ ቤተ ሙከራው ውስጥ በሚገኙት የምርምር ክፍሎች የማስተናገድ አቅም እና ምቹነት መሠረት በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው ፤
3. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በቅርሶች ላይ ለሚያከናውኑት የኩሬሽን ሥራ ድጋፍ ሠጪ ሠራተኛ ካስፈለጋቸው ከክ ፍሉ ኩሬተር ጋር በመነጋገር ሲፈቀድላቸው ማሰራት ይችላሉ ፤
4. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ አስፈላጊውን ሁኔታ በማሟላት የሚያጠኑበትን ስብስብ ፎቶግራፍ የማንሳትና ምስል (ካስት) የማግኘት መብት አላቸው ፤
5. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ የቅርስና የሥነ ምድር ናሙና አግባብ ባለው መመሪያ መሠረት ማውጣት ይችላሉ ፤
6. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በፅሁፍ በማሳወቅ ሲፈቀድላቸው የቤተ ሙከራ ጥናት ጊዜያቸውን ማራዘም ወይም ማቋረጥ ይችላሉ ፤
7. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በቤተ ሙከራ ለመገልገል ክፍያ ለፈፀሙባቸው ቀናት ሁሉ ተገቢውን አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፤
8. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ ከመንግሥት የሥራ ሰዓት ውጭና በበዓላት ቀናት ደንብና መመሪያውን ተከትለው የመገልገል መብት አላቸው ፤
9. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ የጥናትና ምርምር ውጤታቸውን ደንብና መመሪያውን ተከትለው የማሳተም መብት አላቸው።
10. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ የአዳዲስ ግኝቶችን ጥናት በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ባያጠናቅቁ እንደ ቅርሱ ሁኔታና በባለሙያዎች ታይቶ የላቦራቶሪ ጥናቱ ለሁለት አመት ሊራዘምላቸው ይችላል።
11. ተመራማሪዎች ለቤተ ሙከራ ጥናታቸው አጋዥ የሆኑ ቁሳቁሶችን ወደሀገር ውስጥ ሲያስገቡም ሆነ ከሀገር ሲያስወጡ ከዳይሬክቶሬቱ የድጋፍ ደብዳቤ የማግኘት መብት አላቸው።

## 9. <u>የተመራማሪዎች ግዴታ</u>

1. አንድ ተመራማሪ/ቡድን በቤተ ሙከራ ሲያጠና ተመራማሪው/ቡድኑ ለሚያጠናቸው ቅርሶችም ሆነ ለሚገለገልባቸው ንብረቶች ሃላፊነቱን ይወስዳል ፤
2. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ ሊያሰሯቸው የሚፈልጓቸው የቅርስ ዝግጅት ሰራተኞች የባለሥልጣኑ ቋሚ ሠራተኞች ካልሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚያዘጋጅላቸውን ጊዜያዊ ባጅ በመቀበልና ሙሉ ኃላፊነቱን በመውሰድ በተወሰነላቸው ክፍል ውስጥ ብቻ እንዲሰሩ ማድረግ አለበት፤
3. የጥናት ቡድኑ መሪ የቅርስ ዝግጅት ቴክኒሽያኖች ለሚሰሩበት ቅርስም ሆነ የድርጅቱ መገልገያ መሣሪያ ሃላፊነቱን ይወስዳል ፤
4. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በሚሠሩበት ክፍል ለሚጠፋው ንብረት በወቅቱ ዋጋ መሠረት እጥፉን ይከፍላሉ ፤
5. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ሞልዶችን ከቤተ ሙከራው ማውጣት አይችሉም፡፡በተጨማሪም የሚያስነሱትን ወይም የሚያነሱትን የቅርስ ፎቶግራፍ ወይም የሚያሰሩትን ሳይንሳዊ ካስት በስምምነታቸው መሠረት ለሳይንሳዊ ጥናት ብቻ የማዋል ፤ለንግድ ተግባር ያለማዋልና ለሶስተኛ ወገን ያለማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው ፤
6. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ የጥናታቸውን ውጤት በህትመት ሲያወጡ አምስት ቅጅዎችን /ኮፒዎችን/ ለባለስልጣኑ መስጠት ይኖርባቸዋል ፤
7. ተመራማሪዎች/አጥኚዎች/ ያለፍቃድ ወደስብስብ ክፍሎች መግባትና ጥናት ማካሄድ አይችሉም ፤ ሆኖም ከስብስብ ክፍሉ መውጣት የማይችሉ ቅርሶች ሲኖሩ ኩሬተሩ ባለበት ጥናት ያደርጋሉ ፤
8. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በቤተ ሙከራው በሚዘጋጀው የዕለት ሥራ መዝገብ ላይ ሥራቸውን ከጀመሩበት እስከ አጠናቀቁበት ቀን ድረስ በዝርዝር የሠሩባቸውን ስፐስመኖች ፤ያጠናቀቁትን ጥናትና የጨረሱበትን ቀን ካሰፈሩና ቅርሱን ከመለሱ በኋላ ክሊራንስ መውሰድ አለባቸው፡፡
9. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በተሰጣቸው የጥናት ፕሮጀክት ፍቃድ ከመስክ የሰበሰቧቸውን ቅርሶች አስፈላጊውን የርክክብ ቅድመ ሁኔታ አሟልተው ከጊዜያዊ ማቆያ ክፍል አውጥተው በሚሰጣቸው ቦታ ላይ ማደራጀት ፤ በውሰት የወሰዱትን ቅርስ መመለስ ወይም አስፈላጊ ሲሆን የጊዜ ማራዘም ጥያቄያቸውን ማቅረብ አለባቸው፡፡ይህ ባይሆን ግን ቀጣይ የቤተ ሙከራና የመስክ ስራ ፈቃድ አይሰጣቸውም፡፡
10. ተመራማሪዎች ከሥራ ሰዓት ውጭ የላቦረቶሪ አግልግሎት የሚፈልጉ ከሆነ ፤ በተዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት ጥያቄያቸውን በቅድሚያ ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 10.<u>የኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች የአገልግሎት ክፍያ</u>

1. በፕሮጀክት ያልታቀፉ ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች ለቤተ ሙከራ አገልግሎት ማመልከቻ ቅፅ መሙያ 50 የኢትዮጵያ ብር ይከፍላሉ ፤
2. በግልም ሆነ በቡድን የሚያጠኑ ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች ለቤተ ሙከራ እያንዳንዳቸው በቀን 50 የኢትዮጵያ ብር ይከፍላሉ ፤
3. በግልም ሆነ በቡድን የሚያጠኑ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ከቤተ ሙከራ አገልግሎት ክፍያ ነፃ ይሆናሉ፤

4. በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ይሰሩ የነበሩና በጡረታ የተገለሉ አጥኚዎች የቤተ ሙከራ አገልግሎት ጥያቄ ካቀረቡ በአንድ የጥናት ዘመን ሶስት ወር ከክፍያ ነፃ በሆነ መንገድ ይገለገላሉ ፤ ከዚያ በኋላ ላለው ጊዜ ግን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ይስተናገዳሉ ፣
5. በፕሮጀክት ያልታቀፉ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ ፕሮጀክት ያላቸው ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ ከመስክ የሚሰበስቧቸ ውን ቅርሶች ለማደራጀት ለሁለት ወራት ከክፍያ ነፃ የቤተ ሙከራ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ ፤ነገር ግን የማመልከቻ ቅጽ ክፍያ መክፈል ይጠበቅባቸዋል ፤ ከሁለት ወር በኋላ ለሚያደርጉት ጥናት ግን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ይስተናገዳሉ ፣
6. በፕሮጀክት ያልታቀፉ ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች መስሪያ ኬሚካሉን አቅርበው ካስት /ምስል/ ማሰራት ከፈለጉ በሚያዝዙበት ወቅት ለባለስልጣኑ 50 የኢትዮጵያ ብር የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላሉ፣
7. ሁሉንም ክፍያዎች ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/በኢትዮጵያ ብር በዶላር ወይም በዩሮ ወይም በሌሎች የውጭ ሃገራት ገንዘብ ተመጣጣኙን የዶላር ምንዛሬ በባለስልጣኑ የሂሳብ ባለሙያዎች በኩል ያከናውናሉ ፡፡

**II.** **ኢትዮጵያውያን ላልሆኑ ተመራማሪዎች የአገልግሎት ክፍያ**

**1.** ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ የቤተ ሙከራ አገልግሎት ጥያቄ ሲያቀርቡ ለማመልከቻ ቅፅ መሙያ 50 የአሜሪካ ዶላር ይከፍላሉ ፣

**2.** በግል ለሚያጠኑ የውጭ ሀገር ዜጋ ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ ለቤተ ሙከራ አገልግሎት በቀን 25 የአሜሪካ ዶላር ይከፍላሉ ፤ በቡድን ለሚያጠኑ ደግሞ እያንዳንዳቸው በቀን 15 የአሜሪካ ዶላር ይከፍላሉ ፣

**3.** የውጭ ሀገር ዜጋ የሆኑ ተማሪዎች ለቤተ ሙከራ አገልግሎት በቀን 10 የአሜሪካ ዶላር ይከፍላሉ ፣

**4.** ተመራማሪዎች የቅርሶችን ካስት /ምስል / ማሰራት ከፈለጉ በሚያዝዙበት ወቅት ለተቋሙ 50 የአሜሪካ ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ማሰራት ይችላሉ ፣

**5.** ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ከመንግስት የሥራ ሰዓት ውጪ በቤተ ሙከራ ሲሰሩ በሰዓት 5 የአሜሪካ ዶላር፣ ቅዳሜና እሁድ ሲሰሩ በቀን 10 የአሜሪካ ዶላር እንዲሁም በብሔራዊ የበዓላት ቀናት ሲሰሩ በቀን 20 የአሜሪካ ዶላር ወይም የዚህን ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር በወቅቱ የምንዛሪ ዋጋ ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሂሣብ ክፍል በቅድሚያ ገቢ ያድረጋሉ፡የከፈሉበትን ደረሰኝ ቅጅ ለየቅርስ ማሰባሰብ ፣ማደራጀትና ላቦራቶር ዳይሬክቶሬት ያስረክባሉ፡፡

**6.** **የ**መስክ ስራ ፍቃድ ያገኙ የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በፈቃድ ዘመናቸው /በዓመቱ ፈቃዳቸው ውስጥ /ከመስክ የሚሰበስቡትን ቅርስ ለማደራጀት ለሁለት ወራት ከክፍያ ነፃ የቤተ ሙከራ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ ፤ ነገር ግን የማመልከቻ ቅጽ ክፍያ መክፈል ይጠበቅባቸዋል ፣

**7.** በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሁለት ወር ነፃ የቤተ ሙከራ አገልግሎት መጠናቀቅ በኋላ ላለው ጊዜ ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በዚህ ክፍል ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይስተናገዳሉ ፣

8. ሁሉንም ክፍያዎች ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በዶላር ወይም በዩሮ ወይም በሌሎች የውጭ ሃገራት ገንዘብ ተመጣጣኙን የዶላር ምንዛሬ በባለስልጣኑ የሂሳብ ባለሙያዎች በኩል ያከናውናሉ ፡፡

**12.<u>የኩሬተሮች ሃላፊነቶች</u>**

በስበስብ ማዕከሎች መጠን፣በተቋሙ ራዕይና ተልዕኮ እንዲሁም ባለው የሰው ሃይልና የበጀት መጠን ተመስርቶ የኩሬተሮች ሃላፊነት የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡-

1. ጥናትና ምርምር ማድረግ፡-ጥናት ማድረግና በተለያዩ ሕትመቶች የሚወጡ ሙያዊ ፅሁፎች ማዘጋጀት፣
2. የማሕበረሰብ ወይም የሕዝብ ግንኙነት ሥራ፡በተለያየ ደረጃ በሚዘጋጁ ውይይቶች፣ስብሰባዎችና ኮንፈረንሶች ላይ ገለፃ ማድረግ፣የጥናት ውጤቶችን ማሣወቅ፣ተቋሙን መወከልና የሕዝብ ግንኙነት ሥራ መስራት፣
3. ቅርሶችን ማሰባሰብ፣መንከባከብና ፡-አስፈላጊውን ግንዛቤና ቅድመ ሁኔታ በማሟላት ቅርሶች እንዲሰባሰቡ፣እንዲጠበቁና አስፈላጊ ሲሆን እንዲወገዱ በማድረግ ቋሚ ስብስብ መገንባት፣
4. ስብስቦችን ተደራሽ ማድረግ፡-የቅርስ ባለቤቶችና ሌሎች ምንጮችን ጥቅም ባከበረና ያስቀመጡትን ቅድመ ሁኔታ በጠበቀ እንዲሁም ስነምግባርን በተከተለ መንገድ ቅርሶች ተደራሽ እንዲሆኑ መስራት፣
5. የኢግዚቢሽን ስራ መስራት፡-በቋሚም ሆነ በጊዜያዊ መልክ ለሚቀርቡ ኢግዚቢሽኖች ይዘት የመለየት፣ ወካይ ቅርሶችን መምረጥና መግለጫዎችን የማዘጋጀት ስራ መስራት፡፡
6. የተግባርና የንድፈ ሀሳብ ስልጠና መስጠት አለበት፡፡

13.<u>የኩሬተሮች የሙያ ስነ ምግባር</u>

የኩሬተርነት ስራ በሚከተሉት የሙያ ስነ ምግባር ላይ የተመሰረተ ነው፡-

1. ማሕበረሰቡን ማገልገል፡- ለትምህርት፣ጥያቄና ውይይት አስተዋፅኦ በማበርከት ሰፊ እና ጥልቅ የሆነውን የሰው ልጅ ዕውቀት ለሕብረተሰቡ እንዲደርስ ማድረግ፣
2. ተቋምን ማገልገል፡- የተቋሙን የገንዘብ፣የቁሳቁስና ዕውቀት ሃብት በመጠበቅ፣ በአግባቡ በመጠቀም እንዲሁም የተለያዩ ባህሎች፣ሃሶቦችና እምነቶችን በማክበር የመስሪያ ቤቱን ራዕይ ማሳካት፣
3. ሙያውን ማገልገል፡ ዕውቀት፣ታማኝነትና ግልፅነትን በእያንዳንዱ ሙያዊ እንቅስቃሴ መጠቀምና ማዳበር፡፡

**14.<u>የስብስብ ክፍሎችን ስለመጎብኘትና በስብስቦች ላይ ቀረፃ ስለማከናወን</u>**

1. የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር መንግስታት ከፍተኛ ባለስልጣኖች ወይም ለጋሽ አካላት የቤተ ሙከራም ሆነ የተለያዩ ስብስብ ክፍሎችን ከተቋሙ ዋና ሃላፊ ፈቃድ ሲያገኙ መጎብኘት ይችላሉ፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በከፍሎች ላይ የሚደረገው ጉብኝት በሚመለከተው የክፍሉ ባለሙያ ወይም ኩሬተር በኩል መሆን አለበት፡፡

3. በቅርሶች ላይ ለማስተዋወቅም ሆነ ለሌላ ተግባር ለሚደረግ የቀረፃ ስራ ከዋና ሃላፊው የፅሁፍ ፈቃድ በቅድሚያ ማግኘት እና ይህንንም ለስብስብ ክፍሉ ማሳወቅ የሚያስፈልግ ሲሆን በክንውኑም ላይ የክፍሉ ባለሙያ ወይም ኩሬተር መገኘት አለበት፡፡

**15. ለሳይንስ ጥናትና ምርምር የሚሠሩ ካስቶች አገልግሎት**

1. ካስት እንዲሠራላቸው የሚጠይቁ ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ አስቀድመው ለስብስብ ክፍሉ በጽሁፍ ባቀረቡት ማመልከቻ ቅደም ተከተላቸው መሠረት አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ ፤
2. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ ለሚያሰሩት ካስት የሚያስፈልገውን ማንኛውንም የካስቲንግ ማቴሪያል ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ በራሳቸው ወጭ ያቀርባሉ ፤ ሆኖም ግን ባለስልጣኑ ካስት መስሪያ ማቴሪያሉን በሚያቀርብበት ጊዜ ተመራማሪዎች የማቴሪያሉን ዋጋ እና የአገልግሎቱን ክፍያ በመክፈል መውሰድ ይችላሉ ፤
3. ተቋሙ ለተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ የካስት ማቴሪያል ዋጋ የሚያስከፍለው ለዚሁ ተብሎ በሚቋቋመው ኮሚቴ ተመን ሲወጣለት ነው ፤
4. ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ከተለያዩ የጥናት ስፍራዎች /ሳይቶች/ የሰበሰቧቸውን ቅሬተ አካላት ሞልድና ካስት እንዲሠራላቸው በዚህ ክፍል ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተገለፀው አግባብ ሲጠይቁ በስብስብ ክፍሉ በሚሠጠው ትዕዛዝ መሠረት ይሠራላቸዋል ፤
5. የተዘጋጀው ካስት ለተመራማሪው በትዕዛዙ መሠረት ይሠጣል ፤
6. ተመራማሪዎች ተሠርቶ የተሠጣቸውን ካስት ማውጣት እንዲችሉ በዳይሬክቶሬቱ ጽ/ቤት ለሚመለከተው ክፍል ደብዳቤ ይፃፍላቸዋል ፤
7. ተመራማሪዎች ለቀጣይ ጥናታቸው የሚወስዱትን ካስት ለንግድ ሥራ ወይም ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይችሉም ፤
8. ተመራማሪዎች ለሚያሰሩት ካስት የአገልግሎት ክፍያ 50 የአሜሪካ ዶላር መክፈል ይኖርባቸዋል ፡፡

**16. <u>ለዶክመንቴሽን እና አውደ ርዕይ የሚሠጡ የሞልድና ካስት አገልግሎቶች</u>**

1. ለዶክመንቴሽንና ለኤግዚቪሽን ለሚሠሩ ሞልድና ካስቶች በተቋሙ ወይም በመ/ቤቱ በጀት ተይዞ በየዓመቱ በዕቅድ ውስጥ ተካትቶ ይሠራል ፤
2. የተቋሙ የሥራ ክፍሎች ሞልድ/ካስት/ ለማሰራት ሲፈልጉ በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ በተጠቀሰው መሠረት አስቀድመው ለዳይሬክቶሬቱ ጽ/ቤት በማቅረብ ማስፈቀድ አለባቸው ፤
3. ለዶክመንቴሽን በተሠራው ሞልድ የሚሠራው የመጀመሪያው ካስት ዋና ወይም ማስተር ካስት በመሆኑ በተለየ ማስቀመጫ /ካዝና/ ውስጥ የሚቀመጥ ይሆናል ፤ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ካስቱ እንደ ዋናው ቅርስ ስለሚያገለግል ነው ፤
4. የስራ ክፍሎች ለዶክመንቴሽን በተሠራው ሞልድ ለአውደ ርዕይ ካስት ሲፈልጉ በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ በተጠቀሰው መሠረት በተመሳሳይ ሁኔታ ለስብስብ ክፍሉ ቀርቦ መፈቀድ አለበት።

17. <u>የካስት ሽያጭ አገልግሎት</u>

1. ካስት ተሠርቶ በሽያጭ ለመቅረብ ተመራማሪዎች /አጥኚዎች/ በቅርሱ ላይ የሚያካሂዱት ጥናት የተጠናቀቀ መሆን አለበት ፤
2. ለሽያጭ የሚቀርቡ ካስቶችን ተቋሙ የሚያቋቁመው ኮሚቴ የዋጋ ተመናቸውን ያዘጋጃል፤ በካታሎግም ያወጣል፣
3. ማንኛውም ካስት በሚላክበት ጊዜ ገኘው አካል ከተቋሙ ጋር በሚያደርገው የሽያጭ ውል አባዝቶ ለ3ኛ ወገን እንዳያስተላልፍ ስምምነት መግባት አለበት ፤
4. ማንኛውም ካስት ለሽያጭ በሚወጣበት ጊዜ የስፐስሙኑ አይነት ብዛትና መለያ ቁጥር በባህር መዝገብ ተመዝግቦ መስፈር አለበት ፤
5. የካስት ሽያጭ የሚከናውነው የስብስብ ክፍሉ የማዘዣ ፅሁፍ ለማምረቻ ክፍሉ ሲልክና አስፈላጊው ክፍያም ለመከናወኑ ማረጋገጫ ተያይዞ ሲቀርብ ነው ፤
6. የካስት አምራችና ሻጩ ክፍል የተለያዩ ይሆናሉ፡፡

18.<u>የቅርስ መረጃን ማሟላት</u>

1. የቅርስ ስብስብ ክፍል ባለሙያው ወይም ኩሬተሩ በስብስብ ማዕከሉ ውስጥ የሚገኙትንና መረጃቸው የተሟላላቸውን ቅርሶች ለቅርስ ደክመንቴሽን ክፍል መረጃቸውን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣
2. ጉዳት የደረሰባቸው፣መረጃቸው በአግባቡ ያልተሟላላቸው፣ያልፀዱ እንዲሁም የቅርሶቹን አጠቃላይ ደሕንነት አስመልክቶ የስብስብ ክፍሉ ባለሙያ ለቅርስ ዶክመንቴሽን ክፍል በየወቅቱ ሪፖርት ያደርጋል፣
3. ለዶክመንቴሽን የሚሠሩ ሞልዶችና ማስተር ካስቶችም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 መሰረት መረጃቸው ይያዛል፣
4. የስብስብ ባለሙያዎች በየስብስብ ማዕከሉ የሚገኙ ቅርሶችን መረጃ አዘጋጅተው ለዶክመንቴሽን ክፍል የሚያቀርቡበት ጊዜ በአመት አንድ ጊዜ ሆኖ የቅርስ ዶክመንቴሽን ክፍል በሚያወጣው መረሐ ግብር መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፣
5. የቅርስ ዶክመንቴሽን ክፍል የቅርሶችን መረጃዎች በካታሎግ ካርድ፣ በኢንዴክስ ካርድ፣ በኦብጀክ ቅፅ በማደራጀትና ወደ መረጃ ቋት በማስገባት ለተመራማሪዎች፣ ለተማሪዎች እንዲሁም ለተገልጋዮች መረጃዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በቀላሉ፣በተቀላጠፈ ሁኔታ ያቀርባል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**19. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

20. **ቅጣት**

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ ይጠየቃል፡፡

**21. የተሻረ ወይም ተፈፃሚነት የሌለው መመሪያ**

‹የሙዚየም ላቦራቶሪ ለመጠቀም የወጣ የተሻሻለ መመሪያ› በሚል በሐምሌ 1992 ዓ.ም የወጣው መመሪያ እና ማንኛውም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**22. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚመለከተው አካል ሊሻሻል ይችላል፡፡

**23. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ‒‒‒‒‒‒‒ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አሚን አብዱልቃድር**

**የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር**

**-----------ቀን/2005 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ፤**